የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
SOUTHWEST ETHIOPIA PEOPLES REGIONAL STATE PRESIDENT OFFICE

ቁጥር/Ref. NO : ደምኢሕክ/ርመ/060/11-62
ቀን/Date 8 / 11 / 2017

ለ ---ፍሳንና ሰማት---ቢሮ/ጽ/ቤት/ኮሚሽን
---ሚዛን-አማን---

ለ ----------ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት

ጉዳዩ፣ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትን ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ስለመላክ ይሆናል፡፡

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰኔ 30/2017 ዓ.ም 6ኛ ዙር 3ኛ ዓመት 40ኛ መደበኛ ጉባኤ ባካሄደበት ወቅት የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትን ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ ደንብ ላይ በዝርዝር ተወያይቶ አጽድቋል፡፡

ስለሆነም ደንቡ በመስተዳድር ምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል እያሳወኩ የደንቡን ጥራዝ 11 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር!

ዶ/ር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ አሜንች
ም/ርዕሰ መስተዳድር

የደ/ምዕ/ኢትዮጵያ ሕ/ክ/መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
Southwest Ethiopia Peoples Regional State Office of the President

ግልባጭ

ለርዕሰ መስተዳድርና መስተዳድር ም/ቤት ጽ/ቤት

ቦንጋ፣

ለ ፍትህ ቢሮ

ሚዛን አማን፣

ለ ክልሉ ምክር ቤት

ታርጫ፣

ፖ.ሣ.ቁ. 36 ስ.ቁ. 0473312592/2266 ፋክስ ቦንጋ - ኢትዮጵያ
P.O.Box. TEL. Fax Bonga, ETHIOPIA

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት
ደቡብ ምዕራብ ነጋሪት ጋዜጣ
DEBUB MEERAB NEGARIT GAZETA
OF THE SOUTHWEST ETHIOPIA PEOPLES' REGIONAL STATE

ሶስተኛ ዓመት ቁጥር 48/2017 ሰኔ 30 ቀን 2017 ዓ.ም ቦንጋ፣	በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትን ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ	3rd Year No 48/2017 June. 30/2017 E.C Bonga;

ደንብ ቁጥር 48/2017

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግስት የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤትን ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 48/2017 --ገጽ

መግቢያ

በክልሉ እየታየ ያለውን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ከልማት ዕድገትና ከተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር የተመጣጠነ እንዲሆንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት እንዲኖር እንዲሁም የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ በማሻሻል የድህነት ምጣኔን በእጅጉ መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሉ ውስጥ የሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳይን በተቀናጀ መንገድ ለመምራት እና ለመፈጸም የሚያግዙ የተለያዩ ሴክተር ተቋማትንና ባለድርሻ አካላትን ያቀፈ የሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ምክር ቤት ማቋቋም እና ሥልጣንና ተግባሩን በህግ መወሰን በማስፈለጉ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 33/2016 አንቀጽ 47 ንኡስ አንቀጽ (2) ሥር በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 48/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "ክልል" ማለት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ነው።
2. "ቢሮ" ማለት የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ነው።
3. "ምክር ቤት" ማለት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳይን በበላይነት ለመምራት የተቋቋመ አካል ነው።
4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።
5. "የአስተዳደር እርከን" ማለት በክልሉ ውስጥ ያለዉ የዞን፣ የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር ነዉ።

3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴት ጾታንም ያካትታል።

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ደንቡ በክልሉ የአስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

ስለምክር ቤቱ መቋቋም፣ስልጣንና ተግባር

5. መቋቋም

1. የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ከዚህ በኃላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. ምክር ቤቱ በክልሉ ባሉ አስተዳደር እርከኖችም ይደራጃል።
3. የምክር ቤቱ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ በክልሉና በየአስተዳደር እርከኖች ይደራጃል።

6. ዋና ጽሕፈት ቤት

1. የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የምክር ቤቱ ዋና ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።
2. በየደረጃው በሚገኙ ፕላንና ልማት መምሪያ ወይም ፕላንና ልማት ጽህፈት ቤት የምክር ቤቱ ዋና ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።

7. የምክር ቤቱ ተጠሪነት

1. በክልል ደረጃ ያለው የሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ-መስተዳደር ይሆናል፡፡
2. በየደረጃው ባለው የአስተዳደር እርከን የሚገኙ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ተጠሪነቱ በየአስተዳደር እርከኑ ለሚገኝ ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል፡፡

8. የክልል ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባላት

የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር---------- ሰብሳቢ፣
2. የክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ኃላፊ ---------- ፀሐፊ፣
3. የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ----------አባል፣
4. የክልሉ የጤና ቢሮ ኃላፊ ----------አባል፣
5. የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
6. የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
7. የክልሉ ሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ----------አባል፣
8. የክልሉ ደን፣አከባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለዉጥ ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
9. የክልሉ መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ----------አባል፣
10. የክልሉ ዉሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
11. የክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
12. የክልሉ አርብቶ አደርና ቆላማ አካባቢ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ----------አባል፣
13. የክልሉ ሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
14. የክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
15. የክልሉ ሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ---------- አባል፣
16. በክልሉ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲ ኘሬዝዳንቶች---------- አባል፣
17. የክልሉ ሀይማኖት መሪዎች ፎረም ሰብሳቢ---------- አባል፣
18. የክልሉ ወጣቶች ፌዴሬሽን ኘሬዝዳንት---------- አባል፣
19. የክልሉ ሴቶች ፌዴሬሽን ኘሬዝዳንት---------- አባል፣
20. የርዕሰ-መስተዳድሩ ልዩ አማካሪ ----------አባል፣
21. በምክር ቤት ውሣኔ ሌሎችም መሥሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

9. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

1. በክልሉ የሚካሄዱትን የሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮችን በበላይነት ያስተባብራል፤ይመራል፡፡
2. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሥነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮችን በዕቅዳቸዉ አካተዉ እንዲተገብሩ ያስተባብራል፡፡
3. በሥነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮች የማህበረሰቡንና አመራር አካላትን ግንዛቤ ለማሳልበት የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎች መሠራታቸዉን ይከታተላል፡፡
4. የሥነ-ሕዝብና ልማት ኘሮግራም እንዲዘጋጅ ለምክር ቤት አባል መሥሪያ ቤቶች አመራር ይሰጣል፤የተዘጋጀውን ኘሮግራም ያፀድቃል፤የአፈጻጸም ሪፖርት መርምሮ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል፡፡
5. የክልሉ የሥነ-ሕዝብና ልማት ሥራዎች አተገባበር ችግር ከገጠመው ጉዳዩን አጥንቶ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል፡፡
6. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ለአፈፃፀሙ የሚረዱ የአሰራር መመሪያዎችና ማንዋሎች ያወጣል፡፡
7. የሥነ-ሕዝብና ልማት እንቅስቃሴ ለማበረታታት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡
8. በየአስተዳደር እርከኑ ያሉ ምክር ቤቶች የሥነ-ህዝብና ልማት ፕሮግራም ያፀድቃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

10. የዞን የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባላት

1. የዞን ዋና አስተዳዳሪ----------ሰብሳቢ፤
2. ፕላንና ልማት መምሪያ ኃላፊ----------ፀሐፊ
3. ፋይናንስ መምሪያ ኃላፊ----------አባል፤
4. የጤና መምሪያ ኃላፊ ----------አባል፤
5. ትምህርት መምሪያ ኃላፊ----------አባል፤
6. የግብርና፤ ደን አካባቢ ጥበቃና ህብረት ሥራ ልማት መምሪያ ኃላፊ----------አባል፤
7. የሴቶች፤ህጻናት፤ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ----------አባል፤
8. የሥራና ክህሎት መምሪያ ኃላፊ----------አባል
9. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ኃላፊ----------አባል፤
10. የዉሃ፤ ማዕድንና ኢነርጂ መምሪያ ኃላፊ----------አባል፤
11. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ኃላፊ ----------አባል፤

12. የሠላም፣ ፀጥታና ሚሊሻ መምሪያ ኃላፊ ----------አባል፣
13. የዞኑ ሃይማኖት መሪዎች ፎረም ሰብሳቢ----------አባል፣
14. የዞኑ የሴቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ ----------አባል፣
15. የዞኑ የወጣቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ- ----------አባል፣
16. በዞኑ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ውሣኔ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች መስሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶች አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

11.የዞኖች የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. ምክር ቤቱ በዞኑ የሚካሄዱ ሥነ-ሕዝብ ነክ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል።
2. በዞኑ የሚካሄዱትን የሥነ-ሕዝብ እንቅስቃሴዎች ኘሮግራም ሰነድ እንዲዘጋጅ ለምክር ቤት አባል መሥሪያ ቤቶች አመራር ይሰጣል፤ ያፀድቃል፤ በፀደቀው ኘሮግራም መሠረት ፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው እንዲተገብሩት አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ በሚቀርብለት የአፈጻጸም ሪፖርት መሠረት መርምሮ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል።
3. በዞኑ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች አፈጻጸም ላይ ለሚያጋጥመዉ ችግር ጥናት ያካሄዳል፤ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል።
4. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን ለመተግበር የሚያስችሉ ማስፈፀሚያ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።
5. ለዞኑ አስተዳደር ምክር ቤትና ለክልል ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ሪፖርት በጽሁፍ ያቀርባል።

12.የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባላት

1. የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ /የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ/ ----------ሰብሳቢ፣
2. ፕላንና ልማት ጽህት ቤት ኃላፊ----------ፀሐፊ፣
3. ፋይንንስ ጽህፈት ቤት ኃላፊ----------አባል
4. የጤና ጽህፈት ቤት ኃላፊ----------አባል፣
5. የትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ----------አባል፣
6. የግብርና፤ ደን አከባቢ ጥበቃና ህብረት ሥራ ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊ----------አባል፣
7. የሥራና ክህሎት ጽ/ቤት ኃላፊ----------አባል
8. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ኃላፊ----------አባል፣
9. የዉሃ፣ ማዕድን እና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት ኃላፊ----------አባል፣
10.የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጽህፈት ኃላፊ----------አባል፣

የደ/ምዕ/ኢትዮጵያ ሕ/ክ/መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት Southwest Ethiopia Peoples Regional State Office of the President

11. ሠላምና፣ፀጥታና ሚልሻ ጽህፈት ኃላፊ ----------አባል፣
12. የሴቶች ህጻናት ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ኃላፊ ---------- አባል፣
13. የሃይማኖት መሪዎች ፎረም ሰብሳቢ.----------አባል፣
14.የወጣቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ.----------አባል፣
15. የሴቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ. ----------አባል፣
16. በወረዳውና በከተማ አስተዳደር ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ውሣኔ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አካላት ወይም መ/ቤቶችም አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

13. የወረዳና የከተማ አስተዳደር ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ተግባርና ሀላፊነት

1. በወረዳው /በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል።
2. የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ሰነድ እንዲዘጋጅ ለሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መሥሪያ ቤቶች አመራር ይሰጣል፤ ኘሮግራሙን ያፀድቃል፤ በፀደቀው ኘሮግራም መሠረት ፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው እንዲተገብሩት አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ በሚቀርብለት የአፈጻጸም ሪፖርት መሠረት መርምሮ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል።
3. በወረዳዉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች አፈጻጸም ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ጥናት ያካሄዳል፤ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል።
4. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን ለመተግበር የሚያስችሉ ማስፈፀሚያ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።
5. ለወረዳው/ለከተማ አስተዳደሩ ሥነ-ህዝብ ምክር ቤት እንዲሁም ለዞኑ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ሪፖርት በጹሁፍ ያቀርባል።

14. በየአስተዳደር እርከኑ የም/ቤቱ የግንኙነት አግባብ

1. ምክር ቤቱ በክልል ደረጃ በዓመት ሁለት ጊዜ፤በዞን ደረጃ በዓመት አራት ጊዜ፤ በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ደረጃ በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።
3. የምክር ቤቱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የሆነ እንደሆነ በሰብሳቢው የተደገፈዉ ሀሳብ አብላጫ ድምጽ ይኖረዋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የክልሉ የሥነ-ህዝብ ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

ክፍል ሶስት

የሥነ- ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አወቃቀር፣ተግባርና ኃላፊነት

15. የክልል የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሥነ ህዝብ ምቤት ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

1. የፕላንና ልማት ቢሮ ም/ቢሮ ኃላፊና የመረጃ አስተዳደር ሥርዓትና ሥነ ህዝብ ልማት ጉዳዬች ዘርፍ ኃላፊ---------- ሰብሳቢ
2. የፕላንና ልማት ቢሮ የሥነ-ሕዝብና ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር----------አባል፣
3. የጤና ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር--------አባል፣
4. የትምህርት ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር----አባል፣
5. የግብርና ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር--------አባል፣
6. የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር ----------አባል፣
7. የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር----------አባል፣
8. የሥራና ክህሎት ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር-------
---------- አባል፣
9. ደን፣ አከባቢ ጥበቃና አየር ንብረት ለዉጥ ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር ----------አባል፣
10. የዉሃ፣ ማዕድንና ኢኔርጂ ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር----------አባል፣
11. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ዳይሬክተር ----------አባል፣
12. በሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ዳይሬክተር----------አባል፣
13. በክልሉ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች የጥናት፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ባለሙያ---------አባል፣
14. የክልሉ ወጣቶች ፌዴሬሽን ተወካይ----------አባል፣
15. የክልሉ ሴቶች ፌዴሬሽን ተወካይ ----------አባል፣

የደ/ም ዕ/ኢ ትዮጵያ ሕ/ክ/መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
Southwest Ethiopia Peoples Regional State Office of the President
CamScanner

16. የክልሉ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን በመወከል በተቀናጀ ሁኔታ የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችን ለመሥራት እንዲቻል ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋል፤ ስልቶችን በጋራ ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
2. በሁሉም የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አጋር መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ተግባራዊ የሚሆን የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ለነድ ያዘጋጃል፤ በምክር ቤቱ በማስፀደቅ ተግባራዊ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፡፡
3. የክልሉ ሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም የእኩሌታ ጊዜ ግምገማ እና የፍጻሜ ጊዜ ግምገማ በማድረግ የቀጣይ ሥራ አቅጣጫን ያስቀምጣል፡፡
4. የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በየሴክተር መስሪያ ቤታቸው የልማት ዕቅዶቻቸዉ ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን ሥራዎችን በማካተትና እንዲተገበሩ በዋናነት የሚከታተል ይሆናል፡፡
5. የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ የሥ-ህዝብ ሥራዎች የአፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡
6. በክልሉ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

17. የዞን የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

የዞኑ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞኑ ለሥነ ህዝብ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የፕላንና ልማት መምሪያ የሥነ-ሕዝብና ልማት ቡድን መሪ---------- ሰብሳቢ፣
2. የጤና መምሪያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ-------አባል፣
3. የትምህርት መምሪያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ----------አባል፣
4. የግብርና፣ ደን፣ አካባቢ. ጥበቃና ህብረት ስራ ልማት መምሪያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ----------አባል፣
5. የሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ ----------አባል፣
6. የዉሃ፣ ማዕድን እና ኢነርጂ መምሪያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ---------- አባል፣
7. ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ ----------አባል፣
8. ሥራና ክህሎት መምሪያ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ - ----------አባል፣
9. ሠላም፣ ፀጥታና ሚሊሻ መምሪያ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቡድን መሪ ----------አባል፣

10.የመንግስት ኮምንኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ኮሚኒኬሽን ባለሙያ ----------አባል፣

11. የወጣቶች ፌደሬሽን ተወካይ---------- አባል፣

12. የሴቶች ፌደሬሽን ተወካይ ----------አባል፣

18. የዞን የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የዞኑ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መስሪያ ቤቶችንና ድርጅቶችን በመወከል የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ ለመሥራት እንዲቻል መደያዊና ቴክኒካዊ ዕገዛ ያደርጋል፤ ስልቶችን በጋራ ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡
2. በሁሉም በሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አጋር መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ተግባራዊ የሚሆን የዞኑን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም ያዘጋጃል፤ በሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በማስፀደቅ ተግባራዊ መሆኑን ክትትል ያደርጋል፡፡
3. የዞኑ ሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም የእኩሌታ ጊዜ ግምገማ እና የፍጻሜ ጊዜ ግምገማ በማድረግ ለቀጣይ ሥራ አቅጣጫን ያስቀምጣል፡፡
4. የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በየሴክተር መስሪያ ቤታቸው የልማት ዕቅዶቻቸዉ ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን መካተታቸዉንና መተግበራቸዉን የሚከታተል ባለሙያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡
5. የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ የተከናወኑ ሥራዎች አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ለሥነ ህዝብ ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
6. በዞኑ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትንም ያከናውናል፡፡

19.የወረዳ /የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት

የወረዳው/ የከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሥነ ህዝብ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የፕላንና ልማት ጽህፈት ቤት የሥነ-ሕዝብና ልማት ቡድን መሪ ---------- ሰብሳቢ፣
2. የጤና ጽህፈት ቤት የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ---- --አባል፣
3. የትምህርት ጽህፈት ቤት የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ --አባል፣
4. የግብርና፣ደን ፣አካባቢ ጥበቃና ህብረት ስራ ልማት ጽህፈት ቤት የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ----------አባል፣
5. የሴቶች፣ህጻናት ፣ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ ----------አባል፣
6. ሥራና ክህሎት ጽህፈት ቤት የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ ----------አባል፣

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህ/ክ/መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት Southwest Ethiopia Peoples Regional State Office of the President

7. የዉሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ ----------አባል፣
8. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጽህፈት ቤት የልማት ዕቅድ ዝግጅት ክትትል ግምገማና ግብረ-መልስ ቡድን መሪ----------አባል፣
9. በሠላም፣ ፀጥታና ሚልሻ ጽህፈት ቤት የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ባለሙያ----------አባል፣
10. የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት የኮሚኒኬሽን ባለሙያ----------አባል፣
11. የወጣቶች ፌዴሬሽን ተወካይ ----------አባል፣
12. የሴቶች ፌዴሬሽን ተወካይ ----------አባል፣

20. ወረዳ እና የከተማ አስተዳደር የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የወረዳው/ የከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን በመወከል የስነ- ህዝብ ሥራዎችን በተቀናጀ ሁኔታ ለመሥራት እንዲቻል ሙያዊና ቴክኒካዊ እገዛ ያደርጋል፤ ስልቶችን በጋራ ይቀይሣል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል።
2. በሁሉም የሥነ-ሕዝብ አጋር መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ተግባራዊ የሚሆን የወረዳውን/ የከተማ አስተዳደሩን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም በጋራ ያዘጋጃል፤ በሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በማስፀደቅ ተግባራዊ ያደርጋል።
3. የወረዳውን /የከተማ አስተዳዳሩን የሥነ-ሕዝብ ኘሮግራም የእኩሌታ ጊዜ ግምገማ እና የፍጻሜ ጊዜ ግምገማ በማድረግ ለቀጣይ አካሄድ አቅጣጫን ያስቀምጣል።
4. የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በየሴክተር መስሪያ ቤታቸው የልማት ዕቅዶቻቸዉ ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች መካተታቸዉንና መተግበራቸዉን ክትትል ያደርጋል።
5. የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ የሥነ ህዝብ ሥራዎች የአፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ለወረዳ/ ለከተማ አስተዳደሩ ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ያቀርባል።
6. የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትንም ያከናውናል።

21. በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የቴክኒክ ኮሚቴ የግንኙነት አግባብ

5. የቴክኒክ ኮሚቴ በክልል ደረጃ በዓመት ሁለት ጊዜ፤በዞን ደረጃ በዓመት አራት ጊዜ፤ በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ደረጃ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
6. የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል።
7. የቴክኒክ ኮሚቴ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የሆነ እንደሆነ በሰብሳቢው የተደገፈዉ ሀሳብ አብላጫ ድምጽ ይኖረዋል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

22. በጀት

1. የምክር ቤቱ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል።
2. ምክር ቤቱ በሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታ ባልሆኑ ድርጅቶች በበጀት ሊደገፍ ይችላል።

23. የበጀት ዓመት

የምክር ቤቱ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል።

24. ስለሒሳብ መዛግብት

1. የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶችን በየዓመት በኦዲተር ያስመረምራል።

25. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

26.የመተባበር ግዴታ

በክልሉ ዉስጥ ያለ ማንኛዉም ተቋም ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

27.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

28.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከጸደቀበት ሰኔ 30 ቀን 2017 ዓ ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ቦንጋ
ሰኔ 30 ቀን 2017 ዓ.ም
ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት

ምክትል ርዕሰ መስተዳድር

የደ/ብ/ም ዕ/ኢትዮጵያ ሕ/ክ/መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት
Southwest Ethiopia Peoples Regional State Office of the President

ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ
South West Ethiopia Regional State Plan and Development Bureau

ደምኢህፕቢ 217/2018
ቀን 8/1/2018

ለ 6ቱ ዞን ፕላንና ልማት መምሪያዎች

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የሥነ ህዝብ ምክር ቤት መቋቋሚያ ደንብ ስለመላክ ይሆናል፡፡

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ የሥነ ህዝብ ም/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ጸድቆ በክልል ደረጃ የሥነ ህዝብ ምክር ቤት መቋቋሙ የሚታወቅ ነዉ፡፡ ስለሆነም በተላከዉ ደንብ መሰረት የዞንና ወረዳ/ከተማ ሥነ ህዝብ ም/ቤቶች እንዲቋቋሙ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ታምራት መኩሪያ ዳይኖ
Tamirat Mekuria Dayin
ም/ቢሮ ኃላፊና የልማት መረጃ ሥርዓት
አስተዳደርና የሥነ ህዝብ ልማት
ጉዳዮች ዘርፍ ኃላፊ
Deputy Bureau Head & Head
Of Development Information System
Management & Human Development Affairs

ግልባጭ

- ✓ ለቢሮ ኃለፊ
- ✓ ለመ/ሥ/አ/ር እና ሥነ ህዝብ ዘርፍ
- ✓ ለሥነ ህዝብ ልማት ትምህርትን ቅስቀሳ ዳይሬቶሬት

ፕላንና ልማት ቢሮ

የደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መ/ፕላንና ልማት ቢሮ
S/W/E/P/R/S/Planning & Dev't Bureau

Website: http://www.SWEPRSBOPD.gov.et E-mail
southwestplan&development2017@gmail.com
ፖ.ሣ.ቁ. ኢትዮጵያ ስ.ቁ. 0473354680 ፋክስ ሚዛን አማን -